

# አድዋ

**የአድዋጦርነት፣ አፍሪካዊድል**

***From Oblivion to Memory***

## ከዝግጅት ክፍላችን

የአሥራ  የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዓመታት ውስጥ የአፍሪካን አገራት አውሮፓውያን በተቀራመቱበት ወቅት ኢትዮጵያ  ለብቻዋ ነፃነቷን አስከብራ ኖራለች። ይህንኑ ነፃነት ለማስከበር ከኢጣልያ ጋር  በየካቲት 23 1888 ባደረገችው ጦርነት  የተጎናፀፈችው ታሪካዊ ድል ዓለም አቀፍ በሆነ መልኩ ስለ ኃያልነት፣ ስለእምቢተኝነትና ስለነፃነት የነበረውን ግንዛቤ የቀየረ ክስተት ነው። በዚያን ወቅት የተለያዩ የአፍሪካ አገራት ቅኝ ግዛትን ለመቃወም ከባድ ተጋድሎ ይደረግ የነበረ ቢሆንም፣ የአድዋን ድል ለየት የሚያደርገው አንድ ቅኝ ገዥ ወራሪ ኃይል መሸነፉ  አውሮፓን በሙሉ ያስደነገጠ ነገር ስለነበር ነው። አውሮፓውያን ከመደንገጥም በላይ የውርደት ስሜትና ለነጭ የበላይነት ስጋት የተሰማቸው ግዜ ነበር። በግዜው የነበሩ ጋዜጦች ይህን ሽንፈት የገለፁት ለማንኛውም ኃያል የአውሮፓ መንግሥት ሊጠብቀው የማይችልና አዋራጅ የሆነ ኩነት እንደነበረ አድርገው ሲሆን፣ ፈረንሣይና ብሪታንያ ደግሞ ይህንን ዜና የኢትዮጵያ ገድል ሳይሆን የኢጣልያ ድክመት እንደሆነ አድርገው አቅርበውታል።

ለማንኛውም የአድዋ ጦርነት በዓለም ዙሪያ በቅኝ ግዥና በባዕድ አገዛዝ ለሚማቅቁ ሕዝቦች ሁሉ ተስፋ ሰጥቶ፣ የዳግማዊ አፄ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ስም ከመቃብር በላይ አኑሯል።

## ሲጀመር

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን  መገባደጃ ዓመታት ላይ ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ተለይታ ዛሬ የአፍሪካ ቀንድ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ውስጥ ብቸኛዋ በነፃነት የምትኖር አገር ነበረች።   ይህ ደግሞ የመልከዓ ምድሯ አቀማመጥ ባለው ስትራቴጂያዊ ፋይዳ ምክንያት አፍሪካ ላይ በሚያደርጉት ቅርምት ወቅት የአውሮፓውያንን ቀልብ ስቦ ነበር። የኢጣልያ ንጉሣዊ መንግሥት በ1863 አንድነቱን ያረጋገጠ ግዛት ከመሠረተ በኋላ ኢጣልያ ከሌሎች የአውሮፓ አገሮች ጋር አቻ ሆኖ ለመታየት እጅጉን የምትጥርበት ግዜ ነበር። ለዚህም ከቀይ ባሕር ጋር አዋሳኝ የሆነው የኤርትራ መሬት አዋጭ መግቢያ ሊሆን እንደሚችል በመገመት በወቅቱ እዚያ አካባቢ የነበሩ የንግድና የፖሊቲካ ሁነቶች በፈጠሩላት አመቺ አጋጣሚ ተጠቅማ ምፅዋ ላይ ሰፈረች።



አፄ ምኒልክ ዳግማዊ

## ውጥረት፡ ዶግዓሊና አድዋ

ኢጣልያ አንዴ ምፅዋ ከገባች በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት መግፋቷን ቀጥላ የኢጣልያ ጦር  በ 1879 ዶግዓሊ ሲደርስ ከራስ አሉላ[1] ጦር ጋር በገጠመው ውግያ ተሸንፎ 500 ወታደሮች ተገደሉበት። ይህ ሽንፈት ለኢጣልያ ውርደት ስለሆነባት ከዚህ በኋላ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለግዛት ማስፋፋት ተልዕኮዋ እንቅፋት ብቻ ሳይሆን፣ የመብቷ ተጋፊ እንደሆነች አርጋ ቆጠረቻት።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በ1882 ከነገሡ በኋላ በመልካም ግንኙነት ዓላማና በበጎ መንፈስ ከኢጣልያ ጋር ያደረጉትን የውጫሌ ስምምነትን ውል የኢጣልያ መንግሥት የጣልያንኛ ትርጉሙን አዛብቶ መፃፉን የተገነዘቡት እቴጌ ጣይቱ ይህን ትርጉም እንደማይቀበሉ አስረግጠው ለጣልያኖቹ ነገሯቸው። በዚህም ምክንያት የተፈጠረው ጠብ ወደ ጦርነት አመራ።

በኢጣልያ ውስጥ የነበረው የፖሊቲካ ሁኔታ ለግዛት ማስፋፋት የተመቸ ነበር። የኢጣልያ መንግሥት በውጭ አገር ግዛት የማስፋፋትን ዓላማ  በዓለም ላይ ያለውን ገናናነት ለማስረፅ ከሚጠቀምበትም በላይ፣ በአገር ውስጥ የገጠመውን ተቃውሞም ማብረጃ እንዲሆንለት ተገለገለበት። ኢጣልያ በነበራት የጦር መሣሪያ ብቃት በመተማመንም ባጭር ግዜ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ድል እንደምትቀዳጅ ወረራው የተካሄደው በእርግጠኛነት ስሜት ነበር።

## ድል



የታሰበው ግን አልሆነም። አፄ ምኒልክ በአሥር ሽዎች የሚቆጠሩ ለአገራቸው ነፃነት የቆሙ አርበኞችን አስከትለው ዘምተው ከሰሜን በኩል የተከሰተው የኢጣልያ ጦር በየካቲት 23 ቀን 1888 ያልጠበቀው ከባድ ተግዳሮት አድዋ ላይ ገጠመው። በዚህ ጦርነት ላይ እቴጌ ጣይቱ አንዷ የጦር አዛዥ ሆነው 5000 የጦር አባላትና 600 ፈረሰኞችን መርተዋል።

## ታሪካዊ ፋይዳ

አንድ የአፍሪካ ጦር ማንኛውንም የአውሮፓ ጦር ድል ይነሳል ተብሎ በማይታሰብበት ዘመን ኢትዮጵያ ይህን ድል በማስመዝገቧ ብዙዎች ተደነቁ። ይህን በማድረጓ ኢትዮጵያ የኢጣልያን የግዛት ማስፋፋት ዓላማ ብቻ ሳይሆን፣ የማናለብኝነት ስሜትም ጭምር ለማርገብ ቻለች ። ይህ የኢትዮጵያ ድል በዓለም በሙሉ ለሚገኙ የአፍሪካ ነፃነት ተሟጋቾችም ሆነ ለጥቁር አሜሪካዊያን የእኩልነት አንቂዎች  የአልበገር ባይነትና የቁርጠኝነት ተምሳሌት ሆነ። ድልና ነፃነት ማንም ሰው መሻትና ማግኘት የሚችላቸው ነገሮች መሆናቸውን ማሳያ ሆነላቸው። የነጭ የበላይነት እንዳይንሰራፋ መታገል እንደሚቻል የታየበት አነቃቂ ክስተት ነበር።

ኢጣልያ በዚህ ሽንፈት የተሰማት ውርደት ቀላል አልነበረም። ስሜን ገናና አድርጌ ታላቅ እሆናለሁ ብላ የተነሳች አገር፣ ያልጠበቀችው ሽንፈት ቁስል ሆነባት ። ይህን ተከትሎ የወጣውም የውጭ ፖሊሲዋ የተመሠረተው በዚህ ያመረቀዘ ቁስል ላይ ነበር።  በ1927 የኢጣልያ የበቀል ስሜትና የመስፋፋት ጉጉት አይሎ ኢትዮጵያ ላይ ሠራዊቷን ባዘመተች ግዜ የፈፀመችው  ግፍ ስፍር ቁጥር የለውም። በየካቲት 12፣ 1929 አዲስ አበባ ላይ የተፈፀመው ግፍ የኢጣልያ መንግሥት ከተለመደው የግዛት ማስፋፋት ዓላማ ባላነሰ፣ ባልሠለጠነና ኋላ ቀር ፖሊቲካ ተነድቶ ሕዝቡ ላይ ሰቆቃ የማድረስ መመሪያ እንደነበረው ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያን በነፃነትና በክብር ለቀጣዩ ትውልድ ከማቆየት ባሻገር የአድዋ ድል ትሩፋት እስከዛሬ ድረስ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ኅብረቀለማት ዓለም አቀፋዊ የጥቁሮች እምቢተኝነትና ነፃነት አድርጎ መትከሉ ነው።



ራስ መኮንንና ሌሎች አርበኞች

(1)ራስ አሉላ እንግዳ (ራስ አሉላ አባነጋ) የመረብ ምላሽ (የዛሬይቱ ኤርትራ) ገዥ በነበሩበት ሰዓት ሁሉም ያከብራቸው የነበሩ አስተዳዳሪ ነበሩ። ከግብፅ ጋር በ 1868ና1869፣ ከሱዳን ማሕዲስቶች ጋር ደግሞ በ 1877ና 1878ከጣልያን ጋር በዶግዓሊ ደግሞ በ1879 ታዋግተው
(2)በስተቀኝ   ሚካኤል ብሩ፣በስተግራ ደግሞ የልዑል ራስ እምሩ አባት የሆኑት ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ አባይነህ ናቸው።
(3)ፊታውራሪ አሉላ ሉልሰገድ በአድዋው ጦርነት በጠላት እጅ ሕይወታቸው አልፏል።



ፊታውራሪ አሉላ ከሌሎች አርበኞች ጋር የጦርነት ዝግጅት ላይ

**ኢትዮጵያን በነፃነትና በክብር ለቀጣዩ ትውልድ ከማቆየት ባሻገር የአድዋ ድል ትሩፋት  እስከዛሬ ድረስ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ኅብረቀለማትን ዓለም አቀፋዊ የጥቁሮች እምቢተኝነትና ነፃነት አድርጎ መትከሉ ነው።**